GOETHE-ZERTIFIKAT A1: START DEUTSCH 1

DURCHFÜHRUNGSBESTIMMUNGEN

የፈተና ሂደትና አፈጻጸም መመሪያ

Stand: 1. September 2025
ሴፕቴምበር 1 2025

Zertifiziert durch
ምስክር ወረቀት በ

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

Durchführungsbestimmungen zur Prüfung GOETHE-ZERTIFIKAT A1: START DEUTSCH 1

Stand: 1. September 2025

Die *Durchführungsbestimmungen* zur Prüfung GOETHE-ZERTIFIKAT A1: START DEUTSCH 1 sind Bestandteil der *Prüfungsordnung des Goethe-Instituts* in ihrer jeweils aktuellen Fassung.
Die *Durchführungsbestimmungen* beschreiben die Bestandteile der einzelnen Prüfungen und regeln die prüfungsspezifischen Bedingungen der Prüfungsorganisation, des Ablaufs und der Bewertung sowie die Berechnung der Prüfungsergebnisse.

Die Prüfung START DEUTSCH 1 wird vom Goethe-Institut getragen. Sie wird an den in § 2 der *Prüfungsordnung* genannten Prüfungszentren weltweit nach einheitlichen Kriterien durchgeführt und bewertet.

Die Prüfung dokumentiert die erste Stufe – A1 – der im *Gemeinsamen europäischen Referenzrahmen für Sprachen (GER)* beschriebenen sechsstufigen Kompetenzskala und damit die Fähigkeit zur elementaren Sprachverwendung.

§ 1 Prüfungsbeschreibung

Siehe hierzu auch *Prüfungsordnung* § 1.

1.1 Bestandteile der Prüfung

Die Prüfung START DEUTSCH 1 besteht aus folgenden obligatorischen Teilprüfungen:
- schriftliche Gruppenprüfung,
- mündliche Gruppenprüfung.

1.2 Prüfungsmaterialien

Die Prüfungsmaterialien bestehen aus *Kandidatenblättern* mit dem *Antwortbogen (Hören, Lesen, Schreiben), Prüferblättern* mit den Bögen *Sprechen – Bewertung*, *Sprechen – Ergebnis* sowie einer Audiodatei.

የጎተ ኢንስቲቱት ሠርተፍኬት አ1: ሰርተፍኬት ዶች 1 (START DEUTSCH 1) የፈተና ሂደትና አፈፃፀም መመሪያ

የወጣባት ቀን፣ ሴፕቴምበር 1 2025

ይህ የጎተ ሰርተፍኬት A1 (START DEUTSCH A1) የፈተናው ሂደትና አፈጻጸም መመሪያ ተሻሽሎ የተዘጋጀ የጠቅላላው የጎተ ኢኒስቲቱት ፈተናዎች ድንጋጌ አንድ አካል ነው።

የፈተና ሂደትና አፈጻጸም መመሪያዎች የእያዳንዱን ፈተና ክፍሎች ያብራራሉ፣ እንደፈተናዎቹ የተለያዩትን የፈተና አፈጻጸም ሂደትና መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎችና የፈተናውን አተራረምና የውጤት አሰጣጥ ይገልጻሉ።

ስታርት ዶች ፈተና አዘጋጅና ባለቤት ጎተ ኢንስቲቱት ነው።
በፈተና ድንጋጌ አንቀጽ 2 መሠረት በመላው ዓለም በሚገኙ የፈተና ማዕከሎች በአንድ ዓይነት መመዘኛ ይከናወናሉ እንዲሁም ይታረማሉ።

በአውሮፓ የጋራ የቋንቋ ችሎታ መመዘኛ መደብ መሠረት A1 ከስድስት ደረጃዎች ውስጥ የመጀመሪያው የቋንቋ ደረጃ ሲሆን ይህም የአንድን ሰው የቋንቋ መጠቀም ችሎታ የጀማሪ ደረጃ ይገልጻል።

አንቀጽ 1 ፈተና አይነት ገለጻ

ለዚህ የፈተና ድንጋጌ አንቀጽ 1 ተመልከት

1.1 የፈተናው ክፍሎች

የጎተ ሰርተፍኬት A1:-ሰርተፍኬት ዶች A1 የሚከተሉትን ግዴታዊ ክፍሎችን ያካትታል፡-
- በቡድን የሚወሰድ የጽሑፍ ፈteና
- በቡድን የሚወሰድ የቃል ፈተና

1.2 የፈተና ቁሳቁስ

የፈተናው ቁሳቁስ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ *የተፈተኝ ደብተር፣ የመልስ መፃፊያ ቅጽ (መስማት፣ማድመጥና መጻፍ) ፣ የፈታኝ ደብተር* ከነመልሱ እንዲሁም *የቃል ፈተና መመዘኛ ቅጽ*፣እንዲሁም *የቃል ፈተና ውጤት መጻፍያ ቅጽ*፣ እና ድምጽ የተቀረጸበት ዳታ

Die *Kandidatenblätter* enthalten die Aufgaben für die Prüfungsteilnehmenden:
- Aufgaben zum Prüfungsteil HÖREN (Teil 1–3);
- Texte und Aufgaben zum Prüfungsteil LESEN (Teil 1–3);
- Texte und Aufgaben zum Prüfungsteil SCHREIBEN (Teil 1 und 2).

የተፈታኞችየፈተና ደብተር የፈተናውን ጥያቄዎች ያካትታል። እነኝህም
- የማድመጥ ፈተና (ከክፍል 1 – 3)
- የንባብ ፈተና (ከክፍል 1 – 3)
- የመፃፍ ፈተና (ከክፍል 1 – 2)

Im Prüfungsteil SPRECHEN erhalten die Prüfungsteilnehmenden Stichwörter und Handlungskarten (Teil 1–3).

በቃል ፈተና ወቅት ተፈታኞች ለመናገር ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ካርዶች ይሰጣቸዋል (ከክፍል 1 – 3)

In den *Antwortbogen* tragen die Prüfungsteilnehmenden ihre Lösungen bzw. ihren Text ein.

በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ የፈተናው ተሳታፊ መልሱን/መልሷን እንዲሁም የጻፈውን/የጻፈችውን ጽሑፍ ያሰፍራል/ታሰፍራለች።

Die *Prüferblätter* enthalten
- die Transkriptionen der Hörtexte;
- die Lösungen;
- die Bewertungskriterien zum Prüfungsteil SCHREIBEN;
- Musterbewertungen zu schriftlichen Leistungsbeispielen;
- die Anweisungen zur Durchführung zum Prüfungsteil SPRECHEN und die Bewertungskriterien.

የአራሚዎች የፈተና ደብተር የሚከተለውን ያካትታሉ፣
- የማድመጥ ፈተና ንግግሮች በፅሁፍ
- መልሶቹን
- የመፃፍ ፈተና መመዘኛዎች
- ለናሙና የታረሙ ፈተናዎች
- የቃል ፈተና ሂደትና ስነ ስርዓት የሚዘረዝር መረጃና የቃል ፈተና የመመዘኛ መመሪያዎች

In den *Antwortbogen* zu den Prüfungsteilen LESEN, HÖREN, SCHREIBEN und in den Bogen *Sprechen – Bewertung* tragen die Prüfenden ihre Bewertung ein.

በመልስ መስጫ ቅጽ ነጥብ መስጫ ቦታ ላይ ፈታኞቹ ለንባብ ፣ ለማድመጥ ፣ ለመጻፍ ክፍሎች እንዲሁም የንግግር ፈተና ውጤት መስጫ ላይ ውጤቱን ይጽፋሉ።

Die Audiodatei enthält die Texte zum Prüfungsteil HÖREN sowie alle Anweisungen und Informationen.

ድምፅ የተቀረጸበት ዳታ የማድመጥ ፈተና ዓይነቱን እንዲሁም መመሪያና መረጃ ይይዛል።

1.3 Prüfungssätze

Die Materialien zu den schriftlichen Prüfungsteilen sind jeweils in *Prüfungssätzen* zusammengefasst. Die Materialien zum Prüfungsteil SPRECHEN können untereinander und mit den schriftlichen *Prüfungssätzen* beliebig kombiniert werden.

1.3 የፈተና ጥራዝ

የፅሑፍ ፈተና ክፍሎች አንድ ላይ መለያ ቁጥር በተሰጣቸው የፈተና ጥራዞች ተካተዋል። የቃል ፈተና ቁሳቁሶችን እርስ በርሳቸው ወይም ከተለያዩ የፅሁፍ ፈተና ጥራዞች ጋር እንዳስፈላጊነቱ ማጣመር ይቻላል።

1.4 Zeitliche Organisation

Die schriftliche Prüfung findet in der Regel vor der mündlichen statt. Falls schriftliche und mündliche Prüfung nicht am selben Tag stattfinden, liegen zwischen schriftlicher und mündlicher Prüfung maximal 14 Tage.

አንቀጽ 1.4 የጊዜ ድርጅት

የጽሑፍ ፈተና በደንቡ ከቃል ፈተና አስቀድሞ ይከናወናል። ምናልባት የጽሑፍ ፈተናውና የንግግር ፈተናው በዕለቱ ካልተከናወኑ በጽሑፍና በቃል ፈተናዎች መካከል ከ14 ቀናት በላይ ማለፍ የለበትም።

Die schriftliche Prüfung dauert ohne Pausen insgesamt 65 Minuten:

የጽሑፍ ፈተናው ያለእረፍት በጠቅላላው በ 65 ደቂቃዎች ይጠናቀቃል፣

Prüfungsteil	Dauer
HÖREN	ca. 20 Minuten
LESEN	25 Minuten
SCHREIBEN	20 Minuten
Gesamt	65 Minuten

የፈተና ክፍል	የሚፈጀው ጊዜ
ማድመጥ	20 ደቂቃዎች አካባቢ
ማንበብ	25 ደቂቃዎች
መጻፍ	20 ደቂቃዎች
ጠቅላላ	65 ደቂቃዎች

Der Prüfungsteil SPRECHEN wird als Gruppenprüfung mit maximal vier Teilnehmenden durchgeführt und dauert 15 Minuten. Es gibt keine Vorbereitungszeit.

የንግግር ፈተናው የቡድን ፈተና ሆኖ ቢበዛ 4 ተሳታፊዎች ይኖሩታል። የፈተናው ጊዜ 15 ደቂቃ ይሆናል። የዝግጅት ጊዜ የለውም።

Für Prüfungsteilnehmende mit spezifischem Bedarf können die angegebenen Zeiten verlängert werden. Einzelheiten sind in den *Ergänzungen zu den Durchführungsbestimmungen: Prüfungsteilnehmende mit spezifischem Bedarf* geregelt.

ልዩ ችግር ላለባቸው ተሳታፊዎች እንደአስፈላጊነቱ የተመደበው ጊዜ ሊራዘም ይችላል። ዝርዝር ሁኔታው *የፈተናው ሂደትና አፈጻጸም መመሪያ ውስጥ ልዩ ችግር ላለባቸው ተሳታፊዎች* (አካለ ስንኩላን) በሚለው አንቀጽ ተደንግጓል።

1.5 Protokoll über die Durchführung der Prüfung

Über die Durchführung der Prüfung wird ein Protokoll geführt, das besondere Vorkommnisse während der Prüfung festhält und mit den Prüfungsergebnissen archiviert wird.

1.5 ስለፈተናው አፈጻጸም ሂደት ቃለጉባኤ

ስለፈተናው አፈጻጸም ሂደት ቃለጉባኤ ይያዛል። ይህ ቃለጉባኤ በፈተናው አፈጻጸም ሂደት ጊዜ የተከሰተ ልዩ ሁኔታ ይመዘግባል። ቃለጉባኤው ከፈተናው ውጤት ጋር ተያይዞ መዝገብ ቤት ይቀመጣል።

§ 2 Die schriftliche Prüfung

Für die schriftliche Prüfung wird folgende Reihenfolge empfohlen: HÖREN – LESEN – SCHREIBEN. Aus organisatorischen Gründen kann die Reihenfolge der Prüfungsteile von den Prüfungszentren geändert werden.

አንቀጽ 2 የጽሑፍ ፈተና

ለጽሑፍ ፈተና የሚከተለው ቅደም ተከተል ይመከራል። ማድመጥ፣ ንባብ፣ መጻፍ፣ በአፈጻጸም ሂደት ምክንያት ይህ ቅደም ተከተል በፈተናው ማዕከል ሊቀየር ይችላል።

Zwischen den Prüfungsteilen ist keine Pause vorgesehen.

በየአንዳንዱ የፈተና ክፍል መካከል እረፍት አይደረግም።

2.1 Vorbereitung

Vor dem Prüfungstermin bereitet der/die Prüfungsverantwortliche unter Beachtung der Geheimhaltung die Prüfungsmaterialien vor. Dazu gehört auch eine inhaltliche Überprüfung inklusive der Audiodatei sowie deren Funktionalität.

2.1 ዝግጅት

ከፈተናው ጊዜ በፊት የፈተናው ኃላፊ የፈተናዎቹን ቁሳቁስ ሚስጢር በመጠበቅ ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣ ይዘታቸውንና ጥራታቸውን ይፈትሻል/ትፈትሻለች። ይሄም የድምጽ ዳታን ያካትታል።

2.2 Ablauf

Vor Beginn der Prüfung weisen sich alle Teilnehmenden aus. Die Aufsichtsperson gibt danach alle notwendigen organisatorischen Hinweise.

Vor Beginn der Prüfung werden die entsprechenden *Kandidatenblätter* und der *Antwortbogen* ausgegeben. Die Teilnehmenden tragen alle erforderlichen Daten auf dem *Antwortbogen* ein; erst dann beginnt die eigentliche Prüfungszeit.

Die *Kandidatenblätter* zu den jeweiligen Prüfungsteilen werden ohne Kommentar ausgegeben; alle Aufgabenstellungen sind auf den *Kandidatenblättern* erklärt.
Am Ende der jeweiligen Prüfungsteile werden alle Unterlagen eingesammelt. Beginn und Ende der Prüfungszeit werden jeweils in geeigneter Form von der Aufsichtsperson mitgeteilt.

Für die schriftliche Prüfung gilt folgender Ablauf:

1. Die Prüfung beginnt in der Regel mit dem Prüfungsteil HÖREN. Die Audiodatei wird von der Aufsichtsperson gestartet. Die Teilnehmenden markieren ihre Lösungen zunächst auf den *Kandidatenblättern* und übertragen sie am Ende auf den *Antwortbogen*.
   Für das Übertragen ihrer Lösungen auf den *Antwortbogen* stehen den Teilnehmenden circa 5 Minuten innerhalb der Prüfungszeit zur Verfügung.

2. Anschließend bearbeiten die Teilnehmenden die Prüfungsteile LESEN und SCHREIBEN in der von den Teilnehmenden gewünschten Reihenfolge. Die Teilnehmenden markieren bzw. schreiben ihre Lösungen zunächst auf den *Kandidatenblättern* und übertragen sie am Ende auf den *Antwortbogen*.
   Für das Übertragen ihrer Lösungen planen die Teilnehmenden circa 5 Minuten innerhalb der Prüfungszeit ein.

3. Den Text zum Prüfungsteil SCHREIBEN (Teil 2) verfassen die Teilnehmenden direkt auf dem *Antwortbogen*.

§ 3 Der Prüfungsteil SPRECHEN

Die Teile 1, 2 und 3 des Prüfungsteils SPRECHEN dauern jeweils circa 5 Minuten.

2.2 አካሄድ

ከፈተናው በፊት የፈተና ተሳታፊዎች መታወቂያቸውን በማሳየት ማንነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ፈተናውን የሚቆጣጠር/የምትቆጣጠር ፈታኝ ስለፈተናው ሂደት አስፈላጊውን ማብራሪያ ይሰጣል/ትሰጣለች።

ከእያንዳንዱ ፈተና በፊት *የተፈታኝ ደብተሮች ከነመልስ መስጫ ቅጽ* ለተፈታኞች ይታደላሉ። *የመልስ መስጫው ቅጽ* ላይ የፈተናው ተሳታፊዎች አስፈላጊዎቹን መረጃዎች ሁሉ ይጽፋሉ። ይህ ከተጠናቀቀ በኋላ ፈተናው ይጀምራል።

የተፈታኝ ደብተሮች ለተሳታፊዎች ሲታደል ምንም ዓይነት ተጨማሪ ማብራሪያ አይሰጥም። ሁሉም የፈተና ትዕዛዞችና ማብራሪያዎች በ*ተፈታኝ የመልስ መስጫ ደብተር* ውስጥ ሰፍረዋል። እያንዳንዱ የፈተና ክፍል ሲጠናቀቅ ሁሉም የፈተና ወረቀቶች ወዲያው ይሰበሰባሉ። ፈተናውን የሚቆጣጠረው/የምትቆጣጠረው ፈታኝ የፈተናውን መጀመሪያ እንዲሁም መጠናቀቂያ ሰዓት በተገቢው ዘዴ ለተፈታኞቹ ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

የጽሑፍ ፈተናው በሚከተለው አካሄድ መሠረት ይከናወናል፡-

1. እንደደንቡ ፈተናው በማድመጥ ፈተና ይጀመራል። የማድመጥ ፈተና የተቀረጸበትን ዳታ፣ ፈተናውን የሚቆጣጠረው/ የምትቆጣጠረው ፈታኝ ይጀምራል/ትጀምራለች። ተሳታፊዎቹ መልሶቻቸውን በቅድሚያ *የፈተና ደብተሮቻቸው* ውስጥ ምልክት ያደርጋሉ፣ በመጨረሻ *የመልስ መፃፊያ ቅጽ* ላይ ያሰፍሩታል።
   ከደብተሩ ወደ *መልስ መጻፊያ ቅጽ* ለማስፈር በዚያው በተመደበው የፈተና ጊዜ ውስጥ 5 ደቂቃ ይኖራቸዋል።

2. ከዚህ ቀጥሎ የንባብ እና የመፃፍ ፈተናዎች ተሳታፊዎቹ በሚመቻቸው ቅደም ተከተል ይሰራሉ። ተሳታፊዎቹ መልሶቻቸውን በቅድሚያ *የፈተናው ደብተሮቻቸው* ውስጥ ይጽፋሉ። በመጨረሻ ይህንኑ *የመልስ መጻፊያ ቅጽ* ላይ ይገለብጣሉ።
   ከደብተሩ ወደ መልስ መጻፊያ ቅጽ ላይ ለማስፈር በዚያው በተመደበው የፈተና ጊዜ ውስጥ ተሳታፊዎቹ 5 ደቂቃ ይመድባሉ።

3. ተሳታፊዎች የመጻፍ ፈተና (ክፍል 2) የመልስ ጽሑፉን በቀጥታ የ*መልስ መጻፊያ ቅጽ* ላይ ይጽፋሉ።

አንቀጽ 3 የቃል ፈተና ክፍል

የንግግር ፈተናው ክፍል 1፣2 እና 3 እያንዳንዱ 5 ደቂቃ ይቆያል።

3.1 Organisation

Für die Prüfung steht ein geeigneter Raum zur Verfügung. Tisch- und Sitzordnung werden so gewählt, dass eine freundliche Prüfungsatmosphäre entsteht. Die Zusammenstellung der Gruppe erfolgt nach dem Zufallsprinzip.

Wie in der schriftlichen Prüfung muss die Identität der Teilnehmenden vor Beginn der mündlichen Prüfung, gegebenenfalls auch während der mündlichen Prüfung, zweifelsfrei festgestellt werden.

3.2 Vorbereitung

Es gibt keine Vorbereitungszeit. Die Teilnehmenden erhalten die Aufgabenstellung direkt in der Prüfung.

3.3 Ablauf

Der Prüfungsteil SPRECHEN wird von zwei Prüfenden durchgeführt. Eine/-r der Prüfenden übernimmt die Moderation des Prüfungsteils SPRECHEN.

Für den Prüfungsteil SPRECHEN gilt folgender Ablauf:

Zu Beginn begrüßen die Prüfenden die Teilnehmenden und stellen sich selbst kurz vor. Die Prüfenden erläutern vor Beginn jedes Teiles die Aufgabenstellung und verdeutlichen diese anhand eines Beispiels.

1. In Teil 1 stellen sich die Teilnehmenden nacheinander anhand der Stichworte auf den *Kandidatenblättern* vor. Anschließend werden sie gebeten, ein Wort zu buchstabieren und eine Nummer wiederzugeben.

2. In Teil 2 sprechen die Teilnehmenden miteinander; sie formulieren Fragen und reagieren darauf. In einer Einzelprüfung spricht der/die Teilnehmende mit einem/einer Prüfenden.

3. In Teil 3 formulieren die Teilnehmenden Bitten oder Aufforderungen an die anderen Teilnehmenden und reagieren darauf. In einer Einzelprüfung spricht der/die Teilnehmende mit einem/einer Prüfenden.

Am Ende der Prüfung werden alle Unterlagen eingesammelt.

3.1 ዝግጅት

ለዚህ ፈተና ተስማሚ የሆነ ክፍል ይመደባል። የጠረጴዛና የወንበሮች አቀማመጥ የቃል ፈተናው የሚከናወንበትን ሂደት መልካም እንዲሆን ይረዳል። በቡድኑ የሚፈተኑት ተፈታኞች ምድብ ባጋጣሚ መልክ ይወሰናሉ።

እንደ ጽሑፍ ፈተናው ሁሉ የንግግር ፈተናው ተሳታፊዎች ከፈተናው በፊት መታወቂያቸውን በማሳየት ማንነታቸው እንዲረጋገጥ መደረግ አለበት። እንደአስፈላጊነቱ በፈተናውም ወቅት ማንነታቸውን ለማረጋገጥ ይጠየቃሉ።

3.2 የዝግጅት ጊዜ

የዝግጅት ጊዜ አይኖርም። ለተሳታፊዎቹ የፈተናው ጥያቄዎችና ትዕዛዞች በቀጥታ በፈተናው ሰዓት ይሰጣቸዋል።

3.3 የፈተናው አካሄድ

የቃል ፈተናው በሁለት ፈታኞች ይከናወናል። ከሁለቱ አንዱ/አንዷ ፈታኝ የቃል ፈተናውን ይመራል/ትመራለች።

የቃል ፈተናው የሚከተለውን ዝርዝር አካሄድ ይኖረዋል፣

በመጀመሪያ ፈታኞቹ ተፈታኞቹን ሰላምታ ሰጥተው ራሳቸውን በአጭሩ ያስተዋውቃሉ። ፈታኞቹ ከእያንዳንዱ የንግግር ፈተና ክፍል በፊት ስለሚካሄደው ፈተና በምሳሌ ያስረዳሉ።

1. በዚህ የንግግር ፈተና ክፍል 1 በተዘጋጀው *የፈተና ወረቀት* መሠረት ተሳታፊዎቹ በየተራ ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ።በመጨረሻ የአንድን ቃል ፊደላትን እና ቁጥሮችን እንዲናገሩ ይደረጋል ።

2. በንግግር ፈተናው ክፍል 2 ተሳታፊዎቹ በየተራ እርስ በርሳቸው ጥያቄ ይጠያየቃሉ ለጥያቄው መልስ ይሰጣሉ። ለብቻ የሚፈተን ተፈታኝ ካለ ከፈታኞች አንዱ ከተፈታኙ ጋር እንዲጠያየቅ ይደረጋል።

3. በክፍል 3 ተሳታፊው አንድ ነገር እንዲደረግለት/እንዲደረግለት ሌላውን ተሳታፊ ይጠይቃል/ትጠይቃለች ወይንም ይለምናል/ትለምናለች።ለብቻ የሚፈተን ተፈታኝ ካለ ከፈታኞች አንዱ ከተፈታኙ ጋር እንዲነጋገር ይደረጋል

ፈተናው ሲጠናቀቅ ሁሉም ወረቀቶችና መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

§ 4 Bewertung schriftliche Prüfung

Die Bewertung der schriftlichen Prüfungsteile findet im Prüfungszentrum oder in ausgewiesenen Diensträumen statt. Die Bewertung erfolgt jeweils durch zwei unabhängig Bewertende. Auf dem *Antwortbogen* werden in dem Feld *Ergebnis (Hören + Lesen + Schreiben)* die erreichten Punkte der Prüfungsteile HÖREN, LESEN und SCHREIBEN zusammengeführt und als rechnerisch richtig gezeichnet.
Die Ergebnisse aus der schriftlichen Prüfung werden nicht an die Prüfenden der mündlichen Prüfung weitergegeben.

አንቀጽ 4 የጽሑፍ ፈተና ዕርማት

የጽሑፍ ፈተናው እርማት የሚካሄደው በፈተና ማዕከል ወይም ለዚህ ተግባር ተገቢ በሆኑ ቢሮዎች ውስጥ ይሆናል። እርማቱ በ2 አራሚዎች በተናጥል ይከናወናል። *በመልስ መስጫ ወረቀት* አጠቃላይ ውጤት (ማዳመጥ + ማንበብ + መጻፍ) በሚለው ቦታ ላይ *የማድመጥ፣ የንባብ፣ የፅሁፍ* ውጤት አንድ ላይ ተደምሮ ይጻፋል። ድምሩ ትክክል መሆኑን ሁለተኛው አራሚ በፊርማ ያረጋግጣል።
የጽሑፍ ፈተናው ውጤት ለንግግር ፈተና ፈታኞች አይሰጥም።

4.1 HÖREN

Im Prüfungsteil HÖREN sind maximal 15 Punkte erreichbar. Es werden nur die vorgesehenen Punktwerte vergeben, pro Lösung 1 Punkt oder 0 Punkte. Zur Berechnung des Ergebnisses werden die vergebenen Punkte addiert.
Die erzielten Punkte werden auf dem *Antwortbogen* im Feld *Ergebnis Hören* eingetragen und von beiden Bewertenden gezeichnet.

4.1 ማድመጥ

በማድመጥ ፈተና የሚገኘው ከፍተኛ ነጥብ 15 ነው። ነጥቦች የሚሰጡት አስቀድሞ በተዘጋጀ የነጥብ አሰጣጥ መመዘኛ መሠረት ብቻ ነው፣ ለአንድ ጥያቄ 1 ወይም 0 ነጥብ ይሰጣል። አጠቃላይ ነጥቦች ተደምረው *በመልስ መስጫ ወረቀት የማድመጥ ውጤት* በሚለው ቦታ ላይ ይጻፋና በሁለቱም ፈታኞች ይፈረማል።

4.2 LESEN

Im Prüfungsteil LESEN sind maximal 15 Punkte erreichbar. Es werden nur die vorgesehenen Punktwerte vergeben, pro Lösung 1 Punkt oder 0 Punkte. Zur Berechnung des Ergebnisses werden die vergebenen Punkte addiert.
Die erzielten Punkte werden auf dem *Antwortbogen* im Feld *Ergebnis Lesen* eingetragen und von beiden Bewertenden gezeichnet.

4.2 ንባብ

በንባብ ፈተና የሚገኘው ከፍተኛው ነጥብ 15 ነው። ነጥቦች የሚሰጡት አስቀድሞ በተዘጋጀ የነጥብ አሰጣጥ መመዘኛ መሠረት ብቻ ነው፣ ለአንድ ጥያቄ 1 ወይም 0 ነጥብ ይሰጣል። አጠቃላይ ነጥቦች ተደምረው *በመልስ መስጫ ወረቀት የንባብ ውጤት* በሚለው ቦታ ላይ ይጻፋና በሁለቱም ፈታኞች ይፈረማል።

4.3 SCHREIBEN

Zur Berechnung des Ergebnisses des Prüfungsteils SCHREIBEN werden die für Teil 1 und 2 vergebenen Punkte addiert. Die erzielten Punkte werden auf dem *Antwortbogen* eingetragen.

4.3 ጽሑፍ

የጽሑፍ ፈተናውን ውጤት ለማስላት በክፍል 1 እና 2 የተገኙት ነጥቦች ይደመራሉ። ውጤቱን ሁለቱም አራሚች *የመልስ መስጫ ወረቀት* ላይ ካሰፈሩት በኋላ የአራሚ ቁጥራቸውን እና ስማቸውን ጽፈው ይፈርማሉ።

4.3.1 SCHREIBEN, Teil 1

In Teil 1 sind maximal 5 Punkte erreichbar.
Es werden nur die vorgegebenen Punktwerte vergeben, pro Lösung 1 Punkt oder 0 Punkte.

Zur Berechnung des Ergebnisses von Teil 1 werden die vergebenen Punkte addiert. Die Bewertungen werden auf dem *Antwortbogen* eingetragen.

4.3.1 ጽሁፍ፣ ክፍል 1

በክፍል 1 የሚገኘው ከፍተኛ የነጥብ 5 ነው። ነጥቦች የሚሰጡት አስቀድሞ በተዘጋጀ የነጥብ አሰጣጥ መመዘኛ መሠረት ብቻ ነው፣ ለአንድ ጥያቄ 1 ወይም 0 ነጥብ ይሰጣል።

የክፍል 1 ውጤትን ለማስላት የተሰጡት ነጥቦች ይደመራሉ። ውጤቱ *የመልስ መስጫ ወረቀት* ላይ ይሰፍራል።

4.3.2 SCHREIBEN, Teil 2

Teil 2 wird von zwei Bewertenden getrennt bewertet, nach festgelegten Bewertungskriterien (s. *Übungssatz*, Teil *Prüferblätter*). Es werden nur die vorgegebenen Punktwerte für jedes der Kriterien vergeben; Zwischenwerte sind nicht zulässig.

In Teil 2 sind maximal 10 Punkte erreichbar. Bewertet wird die Reinschrift auf dem *Antwortbogen*.

Die jeweiligen Punktwerte von Bewertender/-m 1 und Bewertender/-m 2 werden auf dem *Antwortbogen* unter Angabe der jeweiligen Bewerternummer eingetragen. Zur Ermittlung des Ergebnisses zu SCHREIBEN, Teil 2 wird das arithmetische Mittel aus den beiden Bewertungen gezogen und auf volle Punkte gerundet (bis 0,49 wird abgerundet, ab 0,5 wird aufgerundet).

4.3.2 ጽሁፍ፣ ክፍል 2

ክፍል 2ን ሁለቱ አራሚዎች ለየብቻ በተዘጋጀው የእርማት መስፈርት መሠረት ያርማሉ (*የፈታኝን ደብተር፣ የፈተና መለማመጃ* ይመልከቱ።) ለእያንዳንዱ የመመዘኛ መስፈርት በቅድሚያ የተወሰኑት ነጥቦች ብቻ ይሰጣሉ። ከዚህ ውጭ በነዚህ ነጥቦች መካከል ነጥቦች መስጠት አይቻልም።

በ2ኛው ክፍል ከፍተኛው ነጥብ 10 ነው። የሚታረመው በሚነበብ ጽሕፈት *በመልስ መስጫ ወረቀቱ* ላይ የሰፈረው ነው።

አራሚ 1ና እራሚ 2 የሰጡት ነጥቦች *በመልስ መስጫው ወረቅት* ላይ የአራሚ መለያ ቁጥሮቻቸውን በመጻፍ ይመዘገባሉ።የመጨረሻውን ውጤት ለማግኘት ሁለቱ ነጥቦች ተደምረው ለሁለት ይካፈላሉ።(ከ 0,49 ብታች ያሉ ውጤቶች ወድታች ከ0,5 ወደላይ ይጣፈሉ።)

§ 5 Bewertung Prüfungsteil SPRECHEN

Die Teile 1 bis 3 zur mündlichen Produktion werden von zwei Prüfenden getrennt bewertet.
Die Bewertung erfolgt nach festgelegten Bewertungskriterien (s. *Übungssatz*, Teil *Prüferblätter*). Es werden nur die auf dem Bogen *Sprechen – Bewertung* vorgesehenen Punktwerte vergeben. Zwischenwerte sind nicht zulässig.

Im Prüfungsteil SPRECHEN sind maximal 15 Punkte erreichbar, davon 3 Punkte in Teil 1 sowie jeweils 6 Punkte in Teil 2 und 3.

Zur Ermittlung des Ergebnisses des Prüfungsteils SPRECHEN wird aus beiden Bewertungen das arithmetische Mittel gezogen und auf volle Punkte gerundet (bis 0,49 wird abgerundet, ab 0,5 wird aufgerundet). Das Ergebnis des Prüfungsteils SPRECHEN wird auf dem Bogen *Sprechen – Ergebnis* festgehalten und als rechnerisch richtig gezeichnet. Alternativ können die Bewertungen der Prüfenden auch in eine digitale Bewertungsmaske eingegeben werden; unabhängig davon, ob eine papierbasierte oder digitale Prüfung gebucht wurde. Die Prüfenden und Bewertenden authentifizieren sich auf der Testplattform durch individuelle Login-Daten; daher entfällt die Notwendigkeit einer Unterschrift.

አንቀጽ 5 የንግግር ፈተና እርማት

ከ1 እስከ 3 ላሉት የንግግር ፈተና ክፍሎች ሁለቱ አራሚዎች ለየብቻ ነጥብ ይሰጣሉ። አራሚዎቹ በቅድሚያ በተዘጋጀው የማረሚያ መስፈርት መሠረት፣ ያርማሉ። (*የፈታኝ ደብተረን የፈተና መለማምጃን* ይመልከቱ።)
ለእያንዳንዱ የመመዘኛ መስፈርት በቅድሚያ *የንግግር ፈተና ውጤት* ቅጽ ላይ የታቀዱት ነጥቦች ብቻ ይሰጣሉ። በእነዚህ ቀድሞ በተዘጋጁት ነጥቦች መካከል ነጥቦችን መስጠት አይቻልም።

በቃል ፈተና ከፍተኛውን ነጥብ 15 ነው፣ ከዚህ ውስጥ 3 ነጥቦች ከክፍል 1፣ ከክፍል 2 ና 3 ለአያዳዳቸው 6 ነጥቦች ይሰጥሉ።

ውጤቱን ለማስላት ሁለቱ ፈታኞች የሰጡት ነጥቦች ተደምረው መሀከለኛው ነጥብ ይወሰድና ወደ ሙሉ ቁጥር እንዲጠጋጋ ይደረጋል (እስከ 0. 49 ድረስ ወደታችኛው ቁጥር ይጠጋጋል 0.5 ጀምሮ ወደሚቀጥለው ቁጥር ይጠጋጋል)።
የንግግር ፈተና ውጤት *ለቃል ውጤት ቅጽ* ላይ ተመዘግቦ ድምሩ ትክክል መሆኑ በፊርማ ይረጋገጣል ፣
በአማራጭነት የወረቀት ፈተና ሆነ የዲጂታል ፈተና ፈታኞቹ በዲጂታል ማረሚያ ማረም ይችላሉ፣ ፈታኞቹና አራሚዎቹ በግል ባላቸው የመግቢያ ይለፍ ማረጋገጫ መሰረት የፈተናው መስጫ ገበታ ውስጥ ይገባሉ፤ ስለዚህም በእጅ መፈረም አስፈላጊ አይደለም።

§ 6 Gesamtergebnis

Die Ergebnisse der einzelnen schriftlichen Prüfungsteile und das Ergebnis des Prüfungsteils SPRECHEN werden – auch bei nicht bestandener Prüfung – zu einem Gesamtergebnis zusammengeführt.

አንቀጽ 6 አጠቃላይ ውጤት

የእያንዳንዱ የፅሁፍ ፈተና እና የንግግር ፈተና ውጤቶች (ፈተናው ባይታለፍም) *የአጠቃላይ ውጤት ቅጽ* ላይ በተገቢው ሰንጠረዥ ይመዘገባል።

6.1 Ermittlung der Gesamtpunktzahl

Zur Ermittlung der Gesamtpunktzahl werden die in den einzelnen Prüfungsteilen erzielten Punkte mit dem Faktor 1,66 multipliziert und anschließend addiert. Das Gesamtergebnis wird auf volle Punkte gerundet.

6.1 የአጠቃላይ ውጤት ስሌት

የአጠቃላይ ነጥቦቹን ውጤት ለማስላት በእያንዳንዱ የፈተና ዓይነትና ክፍል የተሰጡትን ነጥቦች በ1.66 ይባዛሉ፣ ቀጥሎ አንድ ላይ ይደመራሉ። የጠቅላላው ውጤት ድምር ከተሸራረፈ ወደ ሙሉ ቁጥር ይጠጋጋል።

6.2 Punkte und Prädikate

Die Prüfungsleistungen werden in Form von Punkten und Prädikaten dokumentiert. Es gelten folgende Punkte und Prädikate für die Gesamtprüfung:

6.2 ነጥቦች እና ደረጃዎች

የፈተናው ውጤቶች በነጥቦች እና በደረጃዎች ይመዘገባሉ። የሚከተሉት ነጥቦችና ደረጃዎች የጸኑ ይሆናሉ።

Punkte	Prädikat
100–90	sehr gut
89–80	gut
79–70	befriedigend
69–60	ausreichend
59–0	nicht bestanden

ነጥቦች	ደረጃ
100–90	በጣም ጥሩ
89–80	ጥሩ
79–70	አጥጋቢ
69–60	በቂ
59–0	አልታለፈም

6.3 Bestehen der Prüfung

Maximal können 100 Punkte erreicht werden, 75 Punkte im schriftlichen Teil und 25 Punkte im mündlichen Teil.
Die Prüfung ist bestanden, wenn mindestens 60 Punkte (60 % der Maximalpunktzahl) erreicht und alle Prüfungsteile abgelegt wurden.

Wenn ein/-e Teilnehmende/-r im schriftlichen Teil weniger als 35 Punkte erzielt, ist eine Teilnahme am Prüfungsteil SPRECHEN nicht sinnvoll, da die zum Bestehen notwendige Mindestpunktzahl von 60 Punkten auch bei voller Punktzahl im Prüfungsteil SPRECHEN nicht mehr erreichbar ist.

6.3 ፈተና ማለፍ

ፈተናውን ለማለፍ የሚገኘው ከፍተኛው ነጥብ 100 ሲሆን ለፅሑፍ ፈተናው 75 ነጥብ ለንግግር ፈተና ደግሞ 25 ነጥብ ነው። ፈተናውን ማለፍ የሚቻለው የማለፊያው ነጥብ ቢያንስ 60 ሆኖ ሲግኝና (ከጠቅላላ የነጥብ ቁጥር 60%) ተፈታኙ ሁሉንም ፈተናዎች ሲፈተን ነው ።

አንድ ተሳታፊ በፅሑፍ ፈተና ከ35 ነጥብ በታች ከአገኘ/ከአገኘች የቃል ፈተናው ላይ መሳተፍ ጥቅም የለውም፣ ምክንያቱም በንግግር ፈተናው ከፍተኛውን ነጥብ እንኳ ቢያገኝ/ብታገኝ አጠቃላይ የማለፊያው ዝቅተኛ ነጥብ ላይ መድረስ አይችልም/አትችልም።

§ 7 Wiederholung und Zertifizierung der Prüfung

Es gelten § 14 und § 15 der *Prüfungsordnung*.
Die Prüfung kann nur als Ganzes wiederholt werden.

አንቀጽ 7 ፈተናውን ስለመድገምና የፈተና ማስረጃ ስለማግኘት

የፈተና ድንጋጌ አንቀጽ 14 እና 15 የጸና ይሆናል።
መድገም የሚፈልግ ሰው ሁሉንም የፈተና ክፍሎች መድገም አለበት።

§ 8 Schlussbestimmungen

Diese *Durchführungsbestimmungen* treten am 1. September 2025 in Kraft und gelten erstmals für Prüfungsteilnehmende, deren Prüfung nach dem 1. September 2025 stattfindet.

Im Falle von sprachlichen Unstimmigkeiten zwischen den einzelnen Sprachversionen der *Durchführungsbestimmungen* ist die deutsche Fassung maßgeblich.

አንቀጽ 8 ይህ መመሪያ የጸና የሚሆንበት

ይህ *የፈተና አፈጻጸም ሂደትና መመሪያ* ከሴፕተምበር 1 2025 ጀምሮ የጸና ይሆናል። ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ የሚሆነው ከሴፕተምበር 1 2025 ጀምሮ ለሚፈተኑ ተሳታፊዎች ይሆናል።

የፈተና ሂደትና አፈጻጸም መመሪያ ትርጉም ላይ አከራካሪ ጉዳዮች ከተገኙ የጀርመንኛው ጽሑፍ ወሳኝ ይሆናል።

Legende zu Formatierungen:
VERSAL: Prüfungsnamen und Prüfungsteile (z. B. „Prüfungsteil SPRECHEN“)
kursiv: Dokumentenbezeichnungen, Eigennamen, Verweise (z. B. „Der Bogen *Sprechen – Ergebnis* wird …“)

ANHANG

Zusätzliche Regelungen zur Durchführung digitaler Deutschprüfungen

Digitale Deutschprüfungen werden in Präsenz an einem Laptop des Prüfungszentrums des Goethe-Instituts abgelegt. Abweichend oder zusätzlich zu den oben stehenden Regelungen gilt Folgendes:

1. Abweichend von 1.2 (Prüfungsmaterialien) gilt:

Sämtliches Prüfungsmaterial der Module/Prüfungsteile LESEN, HÖREN und SCHREIBEN wird den Prüfungsteilnehmenden mittels einer Testplattform digital vorgelegt und von diesen digital bearbeitet. Die Prüfungsteilnehmenden verfassen ihre Texte mit einer deutschen Tastatur. Das digitale Material entspricht inhaltlich der papierbasierten Prüfung. Die Übertragung auf Antwortbögen entfällt, da die Prüfungsteilnehmenden ihre Lösungen und ihre Texte direkt auf der Testplattform eingeben. Eine Änderung ihrer Lösungen und ihrer Texte ist so lange möglich, bis das jeweilige Modul bzw. bei nicht-modularen Prüfungen die schriftliche Prüfung abgegeben wurde bzw. die vorgegebene Prüfungszeit abgelaufen ist.

Die Teilnehmenden können am Anfang jedes Moduls bzw. bei nicht-modularen Prüfungen zu Beginn der schriftlichen Prüfung ein Tutorial mit Erklärungen zum Umgang mit der Testplattform ansehen. Die Prüfungszeit startet erst danach.

Die Texte zum Modul/Prüfungsteil HÖREN werden direkt durch die Testplattform über Kopfhörer ausgespielt.

Beim Modul/Prüfungsteil SPRECHEN erhalten die Prüfungsteilnehmenden die Aufgaben weiterhin auf Papier.

Für alle Module/Prüfungsteile können die Prüfungsteilnehmenden bei Bedarf vom Prüfungszentrum gestempeltes Konzeptpapier erhalten.

አባሪ

በዲጅታል ለሚደረጉ ፈተናዎች ተጨማሪ መመሪያ

የዲጂታል ፈተና በላፕቶፕ በፈተና ማዕከሉ የሚሰጥ ነው።ከላይ ከተዘረዘርው በተጭማሪ ውይንም ባፈነገጠ የሚከተለው የጸና ይሆናል።

1 ከ 1.2 ባፈንገጠ (የፈተና ቁሳቁሶች) በሚምለከት የሚከተለው ይጽናል

ሁሉም የፈተና ክፍሎች ወይንም ሞጁሎች ማንበብ፣ማዳመጥ፣መጻፍ፣ በፈተና መስጫ ገበታ (Testplatform) አማካኝነት ዲጂታል ይቀመጡና ይሰራሉ ። ተፈታኞች ጽሑፎችን የጀርመንኛ ፊደላት ባሉት መተየቢያ (ኪቦርድ) ይጽፋሉ ።ይህ በዲጂታል የተዘጋጀው ፈተና በይዘቱ በወረቀት ከሚሰጠው ፈተና ጋር አንድ አይነት ነው ።በወረቀት ፈተና እንደሚደረገው ወደ መልስ መስጫ መገልበጥ አያስፈልግም ። ተፈታኞቹ መልሶቻቸውንና ጽሑፎቻቸውን በቀጥታ በተዘጋጀው የመፈተኛ ገበታ (Testplatform) ላይ ይሰጣሉ። የተሰጡትን መልሶች ለማረም እንዲሁም ጽሑፎቹን ለማስተካከል ፈተናው ጨርሶ እስካልተሰጠና ለፈተናው የተሰጠው የጊዜ ገደብ እስካላለቀ ድረስ ይችላል።

ተፈታኞች ከእያንዳንዱ ሞጁል ወይንም ሞጁል በሌላቸው ፈተናዎችም ቢሆን የጽሑፍ ፈተና ሲጀመር የፈተና መስጫ ገበታውን (Testplatform) እንዴት እንደሚጠቀሙ የሚያስረዳ አጋዥ መመሪያ ከማብራሪያ ጋር መመልከት ይችላሉ። የፈተና ሰዓቱ የሚያጀምረው ከዚያ በኋላ ነው፡
፡

የማድመጥ ፈተና ወይም ሞጁል ከፈተና መስጫ ገበታው (Testplatform) በቀጥታ በጆሮ ማዳመጫ ይከናወናል።

ለቃል ፈተና ተፈታኞች ፈተናውን በወረቀት ይወስዳሉ።

ለሁሉም ሞጁሎች ወይንም የፈተና ክፍሎች ተፈታኞቹ እንደፍላጎታቸው ማስታወሻ ለመያዝ የፈተና ማዕከሉ ማህተም ያረፈበት ነጭ ወረቀት ይሰጥቸዋል።

2. Abweichend von § 4 (Bewertung) gilt:

Die Aufgaben mit vorgegebenen Antwortmöglichkeiten in den Modulen/Prüfungsteilen LESEN und HÖREN werden technisch automatisiert durch die Testplattform bewertet. Bei den Modulen/Prüfungsteilen SCHREIBEN und SPRECHEN werden die Bewertungen durch zwei voneinander unabhängig Prüfende/Bewertende direkt auf der Testplattform eingegeben. Die Bewertungskriterien entsprechen den Bewertungskriterien der papierbasierten Prüfung. Die Prüfenden und Bewertenden authentifizieren sich auf der Testplattform durch individuelle Login-Daten, daher entfällt die Notwendigkeit einer Unterschrift.

2. ከአንቀጽ 4 (እርማት) ባፈንገጠ የሚከተለው ይጸናል

ማንበብና መድመጥ ፈተናዎች ወይንም ሞጁሎች በቀጥታ በፈተና መስጫ ገበታው (Testplattform) ይታረማሉ። የጽሑፍና የመናገር የፈተና ክፍሎች ወይንም ሞጁሎች እርማቶች በሁለት ፈታኞች/አራሚዎች የየግል ምዘና መሰረት ቀጥታ የፈተና መስጫ ገበታው (Testplattform) ውስጥ ይሰጣሉ። የእርማት መመዘኛዎቹ ከወረቀት ላይ ፈተና መመዘኛዎችን *ጋር* አንድ ናችው። ፈታኞች እና አራሚዎች ባላቸው የግል የመግቢያ ይለፍ የፈተና መስጫ ገበታ (Testplattform) ላይ በመግባት ማንነታቸውን ስለሚያረጋግጡ የእጅ ፊርማ አስፈላጊ አይደለም።

Zusätzliche Regelungen zur Durchführung von Online-Deutschprüfungen

Online-Deutschprüfungen werden unter bestimmten Voraussetzungen (vgl. zusätzliche Regelungen in den Anhängen der *Prüfungsordnung* und *Durchführungsbestimmungen*) ortsunabhängig an einem privaten Desktop-Computer oder Laptop abgelegt. Für Online-Deutschprüfungen gilt Folgendes:

በበየን መረብ ለሚደረጉ ፈተናዎች ተጨማሪ ደንቦች

የበየነ መረብ ፈተናዎች በተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች መሰርት ይካሄዳሉ (ይህን በሚመለክት *የፈተና ድንጋጌና የፈተና ሂደትና አፈጻጸምን አብሪዎች* ተመልከት) የበየነ መረብ ፈተናዎች ቦታ ሳይገድባቸው በግል ኮምፒውተር ወይንም ላፕቶፕ ይወሰዳሉ።ለበየነ መረብ ፈተና የሚከተልው ይጽናል፣

1. Abweichend von 1.2 (Prüfungsmaterial) gilt:

Sämtliches Prüfungsmaterial der Module/Prüfungsteile LESEN, HÖREN und SCHREIBEN wird den Prüfungsteilnehmenden mittels einer Testplattform digital vorgelegt und von diesen digital bearbeitet. Das digitale Material entspricht inhaltlich der papierbasierten Prüfung. Die Übertragung auf Antwortbögen entfällt, da die Prüfungsteilnehmenden ihre Lösungen und ihre Texte direkt auf der Testplattform eingeben. Eine Änderung ihrer Lösungen und ihrer Texte ist so lange möglich, bis das jeweilige Modul bzw. bei nicht-modularen Prüfungen die schriftliche Prüfung abgegeben wurde bzw. die vorgegebene Prüfungszeit abgelaufen ist.

1. ከ1.2 (የፈተና ቀሳቁስ) በማፈንገጥ የሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል፣

በአጠቃላይ የፈተናው ሞጁሎቹ ወይንም ክፍሎቹ ቁሳቁስ *ማንበብ፣ ማዳመጥና መጻፍ* በፈትና መስጫ ድር ገጽ (Testplattform) ለተፈታኞች በዲጂታል መልክ ቀርቦ ይሰራል። የዲጂታሉ ፈተና በይዘት በወረቀት ከሚሰጠው አይለይም። ተፈታኞቹ መልሳቸውን በቀጥታ የፈተናው ድረ ግጽ ላይ ስለሚይስገቡ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ መገልበጥ ይቀራል። መልስን መቀየር ወይንም የተጻፈን ጽሑፍ ማረምና መቀየር ፈተናውን ጨርሰው እስከሚይስረክቡ ወይም ለፈተናው የተመደበው ሰዓት እስኪያበቃ ይቻላል።

Die Teilnehmenden können am Anfang jedes Moduls bzw. bei nicht-modularen Prüfungen zu Beginn der schriftlichen Prüfung ein Tutorial mit Erklärungen zum Umgang mit der Testplattform ansehen. Die Prüfungszeit startet erst danach.

ተፈታኞች አንድ ሞጁል ወይንም በሞጁል ለማይሰጡ ፈተናዎች የጽሑፍ ክፍሉ ከመጀመሩ በፊት ስለፈተናው ገለጻ ከተመለከቱ በውኋላ ብቻ ነው የፈተናው ሰዓት የሚጀምረው።

Die Texte zum Modul/Prüfungsteil HÖREN werden direkt durch die Testplattform über den Lautsprecher ausgespielt.

የማደመጥ ክፍሉ ወይንም ሞጁሉ ቀጥታ ከድር ገጹ ላይ በድምጽ ማጉሊያ ይደመጣል።

2. Zusätzlich zu 2.1 (Vorbereitung) gilt:

2.1 Die Prüfungsteilnehmenden verwenden einen Desktop-Computer oder Laptop mit Netzbetrieb, stabiler Internetverbindung, integriertem Mikrofon, integriertem/externem Lautsprecher und integrierter/externer Webcam.

2. ለ2.1 (ዝግጅት) በተጨማሪ የሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል፣

2.1 ተፈታኞቹ የኤልክትሪክ ሶኬት የተሰካበት ፣የማይቋረጥ የኢንተርኔት መስመር፣ አብሮ የተገጠመ ድምጽ መቀበያና ማውጫ እንዲሁም ካሜራ ያልው የጠረጴዛ ኮምፒውተር ወይንም ላፕቶፕ ይጠቀማሉ፣

2.2 Die Tastatursprache ist auf Deutsch eingestellt.

2.2 የመጻፊያ መተየቢያ(ኪ ቦርድ) ባለጀርመንኛ ቋንቋ ነው።

2.3 Die Prüfungsteilnehmenden stellen die Erfüllung der **technischen Voraussetzungen**, die im Folgenden sowie im Buchungsprozess aufgeführt werden, für die Prüfungsdurchführung eigenverantwortlich sicher:

2.3 የፈተና ተሳታፊዎቹ ሲመዘገቡ በሚከተልው የተዘረዘሩትን **የቴክኒክ ቁሳቁስ** በራሳቸው ሃላፊነት ያሟላሉ።

Technische Voraussetzungen:

Gerät:
- Desktop-, Laptop-Computer oder Chromebook
- Sicherheitsüberprüfung und ggf. zweite Kamera: Smartphone

Monitor:
- ein Monitor oder Bildschirm
- mehrere Monitore oder Doppelbildschirme sind nicht zulässig

Lautsprecher/Mikrofon:
- interner oder externer Lautsprecher sowie ein im Computer oder der Webkamera integriertes Mikrofon
- Kopfhörer mit oder ohne eingebautes Mikrofon oder In-Ear-Kopfhörer sind nicht zulässig

Kamera:
- Integrierte Kamera oder eine separate Webkamera
- Hinweis: Die Kamera muss so bewegt werden können, dass die Prüfungsaufsicht einen 360°-Blick auf den Raum, einschließlich der Tischoberfläche und Tischunterseite, erhält.
- Ggf. Smartphone als zweite Kamera

Browser:
- Google-Chrome™-Browser
- Browser des Dienstleisters für die virtuelle Prüfungsüberwachung wird beim Technik-Check und am Prüfungstag bereitgestellt.

Internetverbindung:
- Erforderlich: Upload- und Download-Geschwindigkeit von 5 Mbit/s
- Empfehlung: 10 Mbit/s

2.4 Unmittelbar vor der Prüfungsdurchführung müssen alle Computer-Anwendungen und Programme geschlossen sein, die nicht für die Prüfung relevant sind.

3. Abweichend von 2.2 (Ablauf) gilt:

3.1 Die Prüfungsteilnehmenden sorgen dafür, dass sie die Prüfung in einem störungsfreien Raum mit adäquaten Licht- und Sitzverhältnissen ablegen. Räume mit mehr als einer Tür oder mit großen Glasfronten sind nicht erlaubt.

የቴክኒክ ቅድመ ሁኔታዎች

ቁሳቁስ፣
- የጠረጴዛ ኮምፒውተር ወይንም ላፕቶፕ
- ለአካባቢ ቁጥጥርና አስፋላጊ ሆኖ ከተገኘ ሁለተኛ ካሜራ ወይም ስማርት ስልክ

ሞኒተር፣
- አንድ ሞኒተር ወይንመ ማሳያ
- ከአንድ በላይ ሞኒተር አይፈቀድም

ድምጽ ማጉሊያና ድምጽ ማስተላለፊያ
- የውስጥ ወይንም የውጭ ድምጽ ማጉሊያ ወይንም ከካሜራው ጋር የተሰራ የድምጽ ማስተላለፊያ
- በጆሮ ማዳመጫ አብሮ ያልተገጠመ የድምፅ ማስተላለፊያ ወይንም ጆሮ ላይ የሚሰካ የጆሮ ማዳመጫያና መናገሪያ አይፈቀድም።

ካሜራ፣
- ከየጠረጴዛ ኮምፒውተር ወይንም ላፕቶፕ ጋር የተገጠም ወይንም ከውጭ የሚሰካ ካሜራ
- ማሳሰቢያ፣ ካሜራው 360 ዲግሪ የሚሽከረከር ሙሉ ተፈታኙ ያለበትን ክፍል፣ ጠረጴዛ ላይና ከጠረጴዛ ስር ማየት የሚይሳችል መሆን አለበት።
- አስፈላጊ ከሆነ ስማርት ስልክ እንደ ሁለተኛ ካሜራ

የኢንተርኔት ብራውዘር፣
- ጉግል ክሮም
- የፈተና መወሰጃው ብራውዘር ለፍተሻና ለቲክኒክ ሙከራ በፈተና ቀን ይሰጣል።

የኢንተርኔት መስመር፣
- ግዴታ፣ የመጭንና የማውረድ ፍጥነት 5 ኤም ቢት/በሰከንድ
- ምክር፣ የተሻለ የሚሆነው ባለ 10 ኤም ቢት/ሰከንድ

2.4 ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ማንኛውም ከፈተናው ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም ለፈተናው አስፈላጊ ያልሆነ ማስትግበሪያና ፕሮግራም መዘጋት አለበት።

3. ከ2.2 (ሂደት) በማፈንገጥ የሚከተልው ተፍጻሚ ይሆናል፣

3.1 ተፈታኞቹ ፈተናውን ጸጥታ የሰፈነበት በቂ ብርሃን ያለው ተገቢ መቀመጫና ጠረጴዛ ያለው ክፍል ውስጥ መፈተን እንዳለባቸው ተገንዝበው ቦታ ያዘጋጃሉ። ከአንድ በላይ በር ያልው ሰፋፊ የመስተዋት መስኮቶች ያሉት ክፈል አይፈቀድም።

3.2 Während der Prüfung befinden sich außer dem/der Prüfungsteilnehmenden keine weiteren Personen oder Haustiere im Raum, Tür und Fenster werden geschlossen.

3.2 በፈተናው ሰዓት ከተፈታኝ በቀር ሌላ ሰው ወይንም የቤት እንሰሳ ክፍሉ ውስጥ እንዲገኝ አይፈቀድም። መስኮቶችና በር ይዘጋሉ።

3.3 Zur Sicherstellung, dass während der Prüfung keine weiteren Personen den Raum betreten, müssen Arbeitsplatz und Webcam so ausgerichtet werden, dass der/die Prüfungsteilnehmende und die Tür permanent im Bild sind.

3.3 በፈተናው ሰዓት ከተፈታኙ በቀር በክፍሉ ውስጥ ሌላ ማንም ሰው አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተፈታኙና የክፍሉ በር ፈተናው ተጀምሮ እስኪያበቃ ያለማቋረጥ በካሜራ እይታ ውስጥ መሆን አለባቸው።

3.4 Der Prüfungsplatz wird so eingerichtet, dass die Arbeitsfläche leer ist und sich außer dem Desktop-Computer mit Monitor oder Laptop, Lichtbildausweis, ggf. Tastatur und Lautsprecher keine weiteren Gegenstände auf dem Tisch befinden. Wenn der Arbeitstisch über Schubladen verfügt, müssen diese vor der Prüfung leergeräumt werden. Hierzu erfolgt eine Kontrolle.

3.4 ፈተናው የሚወሰድበት ጠረጴዛ ከጠረጴዛ ኮምፒውተር ወይንም ላፕቶፕ፣ ኪ ቦርድ እንደአስፈላጊነቱ የድምፅ ማጉሊያና፣ የተፈታኝ መታወቂያ በቀር ባዶ መሆን አለበት። ጠረጴዛው መሳቢያዎች ካሉት እነኝህ መሳቢያዎች ከፈተናው በፊት ባዶ መደረግ አለባቸው። ይህም ከፈተናው በፊት ቁጥጥር ይደረግበታል።

3.5 Zur Überprüfung der Einhaltung der Prüfungsbedingungen führt die Prüfungsaufsicht zusammen mit dem/der Prüfungsteilnehmenden eine Überprüfung des Raums per Webcam durch.

3.5 የፈተና አሰጥጥና አወሳሰድ መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የፈተና ተቆጥጥሪው ከተፈታኙ ጋር ክፍሉን በካሜራ ይመረምራሉ።

3.6 Der/Die Prüfungsteilnehmende muss während der ganzen Prüfung erkennbar sein. Das Gesicht und die Ohren des/der Prüfungsteilnehmenden müssen während der gesamten Prüfung sichtbar sein und dürfen nicht verdeckt werden.

3.6 ተፈታኙ/ኟ ፈተናው ተጀምሮ እስኪፈጸም መታየት አለበት/አለባት። ራስን መከለል ወይንም ፊቱን/ቷን መደበቅ አይችልም/አትችልም።

3.7 Smartwatches, analoge Uhren, Schmuckstücke im Gesichtsbereich, Haarschmuck sowie gesichtsnahe Accessoires, wie z.B. Tücher, Schals, Krawatten, dürfen während der Prüfung nicht getragen werden, um zu gewährleisten, dass keine unerlaubten technischen Hilfsmittel benutzt werden.

3.7 ስማርት የእጅ ሰዓት፣ ፊት ላይ የሚደረጉ ጌጣጌጦች፣ የፀጉር ጌጦች ፊት ላይ የሚጠጉ ማጌጫዎች ለምሳሌ እንደነጠላ፣ ሻርፕ፣ ከረባትና ባርኔጣ ማድረግ ያልተፈቀደ የድጋፍ ቁሳቁስ መጠቀም ለመከላከል አይፈቀደም።

3.8 Mobiltelefone und weitere mobile Endgeräte müssen nachweislich ausgeschaltet und außerhalb der Reichweite des/der Prüfungsteilnehmenden deponiert werden.

3.8 የእጅ ስልክና ሌሎች የእጅ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክ መሳሪዎች መጥፈታቸውና ተፈታኝ ከተቀመጠበት/ችበት ርቀው መቀመጣቸው መረጋገጥ አለበት።

3.9 Prüfungsteilnehmende verpflichten sich, die vorbereitenden Schritte zur Prüfungsdurchführung sowie die Hinweise der Prüfungsaufsicht zu beachten und Anweisungen umzusetzen.

3.9 የተፈተና ተሳታፊዎች ለፈተናው ሂደት አስፈላጊ የሆኑትን ዝግጅቶች ለማድረግ ለፈተና ቁጥጥሩ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች የመረዳት የማክበርና የማስፈጸም ግዴታ ይገባል።

3.10 Der schriftliche Teil der Online-Deutschprüfung findet als Einzelprüfung statt. Der Prüfungsteil/Das Modul SPRECHEN wird abhängig von den Gegebenheiten am Prüfungszentrum entweder als Einzel- oder Paarprüfung durchgeführt.
Die zeitliche Organisation der Prüfung erfolgt gemäß 1.4.: Falls während der schriftlichen Prüfung ein Toilettengang erforderlich ist, wird der Zeitplan beibehalten und die Prüfungszeit nicht verlängert.

3.10 በበየን መረብ የሚደረገው የጽሑፍ ፈተና ለብቻ ይወሰዳል። የፈተናው የቃል ሞጁል ወይም ክፍል እንደነባራዊ ሁኔታዎች በፈተና ማዕከሉ ለብቻ ወይንም በጥንድ ይወሰዳል።

የፈተናው የጊዜ አደረጃጀት በ1.4 መሰረት ይፈጸማል። ምናልባት በፈተናው ወቅት ወደመጸዳጃ ክፍል መሄድ ካስፈለገ የፈተናው ጊዜ ይጠበቃል ለዚህም ተጨማሪ ጊዜ አይሰጥም።

4. Abweichend von § 4 und § 5 (Bewertung) gilt:

Die Aufgaben mit vorgegebenen Antwortmöglichkeiten in den Modulen/Prüfungsteilen LESEN und HÖREN werden technisch automatisiert durch die Testplattform bewertet. Bei den Modulen/Prüfungsteilen SCHREIBEN und SPRECHEN werden die Bewertungen durch zwei voneinander unabhängig Prüfende/Bewertende direkt auf der Testplattform eingegeben. Die Bewertungskriterien entsprechen den Bewertungskriterien der papierbasierten Prüfung (siehe dazu § 4 und § 5). Die Prüfenden und Bewertenden authentifizieren sich auf der Testplattform durch individuelle Login-Daten, daher entfällt die Notwendigkeit einer Unterschrift.

4. ከአንቀጽ 4 እና 5 (እርማት) በማፈንገጥ የሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል

ምርጫ ያላቸው ፈተናዎች *ማንበብና ማድመጥ ሞጁሎች ወይንም ክፍሎች* ቀጥታ በፈተናው ድረ ገጽ ይታረማሉ። *መናገርና መጻፍ* ሞጁሎች ወይንም ክፍሎች በሁለት አራሚዎች ለብቻ በቀጥታ ድረ ገጹ ላይ ይታረማል። የማረሚያ መስፈርቶቹ በወረቀት ከሚወሰዱ ፈተናዎች ጋር ልዩነት የላቸውም (ለዚህ አንቀጽ 4ና 5 ተመልከት)። አራሚዎቹና ፈታኞቹ ድረ ገጹ ላይ በግል የሚስጥር ማለፊያ ስለሚገቡ ፊርማ አስፈላጊ አይደለም።

© 2025 Goethe-Institut e.V.
Bereich 41 – DaF-Prüfungen
www.goethe.de/pruefungen